በብራና ፡ ተጽፎ ፡ ገበታው ፡ በብር ፡ ሐረግ ፡ ተከፍፎ ፡ ከደስታ ፡ መግለጫ ፡ ጽሑፋችን ፡ ጋራ ፡ ተጠርዞ ፡ ማስታወሻው ፡ ከመታሰቢያው ፡ ጋራ ፡ ቀር ቧል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ስጦታ ፡ ሰጭ ፡ ለተቀባዩ ፡ ያለውን ፡ ስሜት ፡ የሚያሳይበት ፡ መግ ለጫ ፡ ስለሆነ ፡ የምናቀርበው ፡ ስጦታ ፡ የማይረሳ ፡ ውለታ ፡ ጉታ ፡ የሆ ኑት ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልክ ፡ ቅርጽ ፡ እንዲሆን ፡ መርጠን ፡ ግርማዊነ ትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጭንቅና ፡ መከራ ፡ ፈጥኖ ፡ ደራሽ ፡ ለመሆኑም ፡ ምሳሌ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ እንደሆኑ ፡ እንዲያሳይ ፡ አድርገናል ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ይህ ፡ በዓል ፡ ምንም ፡ በስም ፡ የንግሥ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ቢባል ፡ ዓመቱን ፡ ብቻ ፡ ቁጥሮ ፡ በመድረስ ፡ እንደሚከበረው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ሳይሆን ፡ በአልጋ ፡ ወራሽነት ፡ ከፈጸሙት ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ ያለፈው ፡ ፷፩ ፡ ዓመት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገርዎና ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብዎ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ የተዋጉበት ፡ በዓ ለም ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡ በፍርድ ፡ የተከራከሩበት ፡ አጥቂውን ፡ ጠላት ፡ አባ ረው ፡ የተደመሰሰውን ፡ ነፃነት ፡ የመለሱበት ፡ ጠላት ፡ በግፍ ፡ የወረሰ ውን ፡ የሕዝብዎን ፡ ርስትና ፡ ንብረት ፡ ያስመለሱበት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጥ ንት ፡ ወሰን ፡ የከለሉበት ፡ በጠቅላላውም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ለማ ድረግና ፡ ለማሳወቅ ፡ የደከሙበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ሥራና ፡ ተጋድሎ ፡ ፷፩ኛው ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ነው ።

ጃ ን ሆ ይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ንግሥን ፡ ከሥራና ፡ ከተጋድሎ ፡ ጋራ ፡ አስተባብሮ ፡ ላሳለፈው ፡ ፷፩ ፡ ዓመት ፡ የብር ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ክብር ፡ የተሠራው ፡ ሐው ልት ፡ ለበዓሉ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ አንዱ ፡ የዛሬ ፡ ፷፩ ፡ ዓመት ፡ ግርማዊ ፡ ነትዎ ፡ በከፈተው ፡ ፓርላማ ፡ ሁለተኛው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዲ ኖር ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራውም ፡ መድ ፡ ከዛሬ ፡ ፷ምሮ ፡ ለተተካው ፡ የወ ርቅ ፡ ጊዜ ፡ መክፈቻ ፡ እንዲሆን ፡ በማለት ፡ አገልጋዮችዎ ፡ አስበን ፡ ያቀረ ብነው ፡ ስጦታ ፡ ስለሆነ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲቀበለን ፡ እንለምናለን ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ይህ ፡ ዛሬ ፡ ያቀረብነው ፡ ስጦታ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ ሠራተኞች ፡ ነው ፡ ብንልም ፡ የወሎ ፡ ሕዝብና ፡ ኑጋዴው ፡ በፈቃዱ ፡ አስቦ ፡ ለዚህ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በሚፈቅ ደው ፡ ዓይነት ፡ የሚሠራበትን ፡ ገንዘብ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ የሕ ዝቡን ፡ ቅን ፡ ሐሳብ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲያውቅለት ፡ እየስታወስን ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ጠብቆ ፡ ለ·ንምሳኛው ፡ ዓመት ፡ የወርቅ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሕይወት ፡ እንዲያደርስዎ ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡

ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡

ዕድሜ ፡ ለልዑል ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ወራሴ ፡ መንግሥት ፡

ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ ሠራተኞች ፡ እንዲሁም ፡ የወሎ ፡ ሕዝብ ፡ በጥልቅ ፡ ከልብ ፡ አስባችሁ ፡ በልጄ ፡ አማ ካይነት ፡ ያቀረባችሁልኝ ፡ መታሰቢያ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኝቶኛል ። በጣም ፡ እናመሰግናችኋለን ።

ይህም ፡ መታሰቢያ ፡ እንደ ፡ ጠየቃችሁት ፡ ሁሉ ፡ አንደኛው ፡ በሕግ፡ መምሪያና ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤታችን ፡ ሁለተኛውም ፡ በጽሕፈት ፡ ቤታ ችን ፡ እንደሚቀመጥ ፡ እናደርጋለን ።

519

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፷፩ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ለማክበር ፡ የመጡትን ፡ የዓለም ፡ ጋዜጠኞች ፡ ጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ. ም. በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ በጎንቶ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብለው ፡ ሲያነጋግሩዋቸው ፡ ሳሉ ፡ የፈረንሣይ ፡ ራዲዮ ፡ ዳፅዚዮን ፡ ባልደረባ ፡ ሙሴ ፡ ሻር ፡ አይዝሐቅ ፡ ምስጋናቸውን ፡ በንግግር ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

የዘውድ ፡ በዓላችንን ፡ ክብር ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ሩቅ ፡ ከሆኑ ፡ አገሮች ፡ መጥታችሁ ፡ ዛሬ ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስንቀበላችሁ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ። ወደየአገራችሁ ፡ ያስተላለፋችሁትን ፡ ቃል ፡ በመስማታችን ፡ በሠራችሁት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ለአደረጋችሁልን ፡ መልካም ፡ የአሳብ ፡ አገላለጥ ፡ እናመሰግናችኋለን ።

እንደምታውቁት ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከዓለም ፡ ሩቅ ፡ ነበረች ። ዛሬ ፡ ግን ፡ መገናኛዎች ፡ በመከፈታቸው ፡ በቅርብ ፡ ለመገናኘት ፡ ተችሏል ። ስለዚህ ፡ ለወደፊቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጐብኘት ፡ ለምትመጡት ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ እንቀበላችኋለን ።

520

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ ፷፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ አከባበር ፡ ክብር ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ኤግዚቪሽን ፡ ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፮ ፡ ዓ. ም. በ፫ ፡ ሰዓት ፡ መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

የግርማዊነትዎን ፡ የ፷፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ይህን ፡ የኢዮቤልዩ ፡ ኤግዚቪሽን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃዱ ፡ ሁኖ ፡ ዛሬ ፡ ለመክፈት ፡ እዚህ ፡ በመገኘት ፡ ኤግዚቢሽኑን ፡ ላዘጋጀን ፡ አገልጋዮችዎ ፡ የሚሰማን ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ ይህ ፡ ዐይነት ፡ ኤግዚቢሽን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ሲታይ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሌሎች ፡ ኤግዚቢሽኖች ፡ በየጊዜው ፡ የታዩ ፡ ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ የተዘጋጀበት ፡ ምክንያት ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ ከቀደሙት ፡ ኤግዚቢሽኖች ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ነው ። ደግሞም ፡ የዚህ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ዓላማ ፡ ካለፉት ፡ ኤግዚቢሽኖች ፡ ይበልጥ ፡ ብዙ ፡ ጉዳይ ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘው ፡ ነው ። ከፍ ፡ ያለ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ አስተያየት ፡ አግኝቷል ።

አሥራ ፡ ስምንት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ስለሚገኙበት ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ሊባል ፡ ተችሏል ። ስለዚህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ወዳጆቻችን ፡ ስላደረጉልን ፡ የማበረታቻ ፡ እርዳታ ፡ የኤግዚቢሽኑ ፡ አደራጅዎች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ እንደተሰማን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መግለጽ ፡ የሚያሻ ፡ አይመስለኝም ። ግርማዊነትዎ ፡ ምንም ፡ የሚያውቀው ፡ ቢሆን ፡ ኤግዚቢሽኑ ፡ ይህንን ፡ ታላቅ ፡ ሆኖ ፡ ሊዘጋጅ ፡ የቻለው ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የነጋዴዎች ፡ እርዳታ ፡ ስለተጨመረበት ፡ መሆኑን ፡ ልገልጸው ፡ እወዳለሁ ። በየክፍሉ ፡ አያሌ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ በማድረግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሥራውን ፡ ፕሮግራም ፡ ለማቋቋምና ፡ ጎላፊ ፡ ሆኖ ፡ ኤግዚቢሽኑ ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ወደሚያየው ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ መሪው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መንግሥት ፡ ቢሆንም በኤግዚቢሽኑ ፡ ዕቃዎቻቸውን ፡ የሚያሳዩና ፡ በጠቅላላው ፡ ነጋዴዎች ፡ የፈጸሙት ፡ ሥራና ፡ ያደረጉትም ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፭ኛ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተናና ፡ ደስታ ፡ በተፈራረቀባቸው ፡ ዓመታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወደከፍተኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ጎላፊነት ፡ በመቀበል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ከዛሬ ፡ ሓያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ንግድ ፡ እንዱስትሪና ፡ እርሻ ፡ ትምህርትና ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ እየተስፋፋ ፡ በጠቅላላው ፡ የአገሩ ፡ ሀብት ፡ እየለማና ፡ እየተወደደ ፡ ሕዝብዎም ፡ ኑሮ ፡ እየተሻሻለ ፡ መሄዱን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ።

፮ኛ ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚገኙት ፡ የሀገሪቱ ፡ ሀብቶች ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ መሆናቸውንና ፡ እነሱም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደሚሠሩ ፡ ለማሳየት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተፈጸመውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሊደረግ ፡ የሚችለውን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ አጉልቶ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለተፈጸመው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ኩራትና ፡ ደስታ ፡ የሚገልጽ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ወደፊት ፡ ስለሚጠበቀው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡

መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ብልጽግና ፡ በተወደዱት ፡ ዜጎችዎና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወዳጆቻችን ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ እንደሚያጠነክረው ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

ይህም ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ትእዛዝና ፡ መሪነት ፡ በመከተል ፡ ካለፈው ፡ ይበልጥ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያበረታታን ፡ ነው ። የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ይህንን ፡ የሺኺኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኤግዚቢሽን ፡ እንዲከፍትልንና ፡ እንዲጐበኝልን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ሥር ፡ ቆሜ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰብዎችዎ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የአዲስ ፡ አበባን ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ለመክፈት ፡ በመምጣታችን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህን ፡ ታላቅ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ለማደራጀት ፡ በብዙ ፡ እንደታሰበበትና ፡ እንደተደከመበት ፡ እናውቃለን ። ኤግዚቢሽኑ ፡ በተወደደችው ፡ አገራችን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይረሳውን ፡ የሺኺኛውን ፡ የዘውድ ፡ በዓላችንን ፡ በደስታ ፡ ለማክበር ፡ የሕዝባችን ፡ ምኞት ፡ ያነሣሣው ፡ በመሆኑ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

በጦር ፡ አደጋ ፡ ቆስላ ፡ የነበረችው ፡ አገራችን ፡ ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካደጋው ፡ ጉዳት ፡ ድና ፡ ዛሬ ፡ ይህንን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መንፈስ ፡ የሚያነቃቃ ፡ በደንብ ፡ የተሠራ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ ለማደራጀት ፡ እንዲቻል ፡ መደረጉ ፡ የሕዝባችንን ፡ ሐሳበ ፡ ጽኑነትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትጋት ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ይህ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ ሕዝብን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሐሳብ ፡ የሚያበረታታና ፡ ትምህርትን ፡ የሚሰጥ ፡ ማኅበራዊ ፡ ጥቅም ፡ የሚገኝበት ፡ ድርጅት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ብዙዎች ፡ ሊጐበኙትና ፡ ብዙዎች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይገባል ።

በዚህ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሺኺት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታችን ፡ የተደረገውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በንግድና ፡ በእንዱስትሪ ፡ ረገድ ፡ የተገኘውን ፡ እድገት ፡ ጭምር ፡ በዓለም ፡ ለማሳየት ፡ የሚያስችላቸው ፡ እንደሚሆንና ፡ እንደዚሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባለእንዱስትሪዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ በኢትዮጵያና ፡ በአገራቸው ፡ መካከል ፡ የንግድ ፡ ሥራቸውን ፡ ለማስፋፋት ፡ ያላቸውን ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያስችላቸው ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

የተዘጋጁትን ፡ ዕቃዎችና ፡ ድርጅቶች ፡ ገና ፡ ባንጐበኛቸውም ፡ ይህ ፡ አውን ፡ የምንከፍተው ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ለመሆኑ ፡ የሚበቁ ፡ ማስረጃዎች ፡ ደርሰውናል ። ስለ ፡ ኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ድርጅት ፡ መንግሥታችን ፡ ካደረገው ፡ እርዳታ ፡ በአገራችን ፡ የሚገኙ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ያደረጉት ፡ የሚያስመሰግን ፡ እርዳታ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ በየጊዜው ፡ የንግድን ፡ ሥራዎች ፡ ለማስፋፋት ፡ በሚቻልባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

ኤክስፖዚሲዮኑን ፡ ለመገኰበኘት ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ የመጡት ፡ እንግዶች ፡ በእርሻ ፡ በእንዱስትሪና ፡ በንግድ ፡ ረገድ ፡ የተደረገውን ፡ እርምጃ ፡ በመልካም ፡ ተመልክተውና ፡ ተረድተው ፡ እንዲመለሱ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ተደርጎበት ፡ ይህ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ በዚህ ፡ ተቋቁሞ ፡ እንዲታይ ፡ መደረጉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ በምትራመድበትና ፡ ንግዷን ፡ በምታስፋፋበት ፡ ጊዜ ፡ በኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ የተባበሩት ፡ ከሰሜን ፡ ከደቡብ ፡ ከምሥራቅ ፡ ከምዕራብ ፡ ከአራቱ ፡ የዓለም ፡ ማዕዘን ፡ የመጡት ፡ ያሥራ ፡ ስምንት ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ያላቸውን ፡ እምነትና ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ የሚያስረዳ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ በተባሉት ፡ አገሮችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የሚጠቀሙባቸውን ፡ የንግድ ፡ በሮች ፡ ለመክፈት ፡ የሚያገለግል ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ የኢዮቤልዩ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ ለሰላምና ፡ ለዓለም ፡

ንግድ ፡ ጉዳዮች ፡ ጎብረት ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ተስፋ ፡ ከማድረግ ፡ ጋር ፡ በጅጅኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓላችን ፡ ምክንያት ፡ የተደራጀውን ፡ ይህንን ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ ስንከፍት ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ይህን ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፡ በማደራጀት ፡ የደከሙት ፡ ኮሚቴዎችና ፡ የኮሚቴውን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ነጋዴዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

521

በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኙ ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆች ፡ በማኅተማ ፡ ጋንዲ ፡ ስም ፡ ያቋቋሙትን ፡ የማዋለጃ ፡ ሆስፒታል ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በ፲ ፡ ሰዓት ፡ መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የኮሙኒቴው ፡ ፕሬዚዳንቱና ፡ የሕንድ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደር ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የሕንድ ፡ ኮሙኒቴ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚኖሩት ፡ የሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ ታላቅ ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ለሰብአዊ ፡ ተግባር ፡ የተሠራውን ፡ ሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ጨርሰን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በማበርከት ፡ ሕልማችን ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የነበረን ፡ ምኞት ፡ ተፈጸመ ። ይኸም ፡ ከእናት ፡ አገራችን ፡ ሲወራረስ ፡ የመጣ ፡ ልምድ ፡ ሲሆን ፡ ለዚሁ ፡ ሕንጻ ፡ የነጻነታችን ፡ አባት ፡ የሆኑት ፡ የማኅተማ ፡ ጋንዲ ፡ ስም ፡ በመስጠቱ ፡ ተደስተናል ። በኢትዮጵያ ፡ የሚኖሩት ፡ የሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ (ተወላጆች) ይህን ፡ ሕንጻ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሲያበረክቱ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለሕዝባችን ፡ ለዋለው ፡ ውለታ ፡ ምስጋና ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ አገርና ፡ (ኢትዮጵያ) ሕዝብ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸውን ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

ምስጋናችንን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በአሁኑ ፡ አኳኋን ፡ በመቀበልዎ ፡ የተሰማንን ፡ ከፍተኛ ፡ የምስጋና ፡ ስሜት ፡ በተለይ ፡ ለመጥቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖብናል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሕንድ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ብንሆንም ፡ ሁላችንም ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ሁለተኛ ፡ አገራችን ፡ እንቆጥራታለን ። ተስፋዋንና ፡ ሥጋትዋን ፡ ብልጽግናዋንና ፡ መከራዋን ፡

ተካፋይ ፡ ከመሆናችን ፡ በላይ ፡ ዕድላችን ፡ ከዕድልዋ ፡ (ኢትዮጵያ) ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ እንደሞከርነው ፡ ሁሉ ፡ ለወደፊቱም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማገልገልና ፡ ለአገርዋ ፡ ልማት ፡ ለመሥራት ፡ ዘወትር ፡ ዝግጁ ፡ መሆናችንን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለማረጋገጥ ፡ እንወዳለን ። ይህን ፡ የሆስፒታል ፡ ሕንፃ ፡ ለመሥራት ፡ ሐሳቡ ፡ የመነጨው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመጀመሪያ ፡ እንደራሴ ፡ ሚኒስትራችን ፡ ከነበሩት ፡ ከክቡር ፡ ሳርዳር ፡ ሳንት ፡ ሳንግ ፡ ነው ። እኛም ፡ የሳቸውን ፡ ሐሳብ ፡ በመቀበል ፡ በእኛ ፡ ኮሚቴዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ ጀመርን ። በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ የኢት ብር ፡ ፪፻፷፭ሺህ ፡ ተሰብስቦ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በተሰጠን ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ሕንፃ ፡ ለመሥራት ፡ ቻልን ።

ግርማዊነትዎ ፡ እንደሚያስታውሰው ፡ የዚህ ፡ ሕንጻ ፡ መሠረት ፡ ደንጊያ ፡ እ. ኤ. ቊ. ኅዳር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ.ም. በግርማዊነትዎ ፡ ተጣለ ። ይህም ፡ ሕንጻ ፡ ዛሬ ፡ ሥራው ፡ አልቆ ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ ከውጭ ፡ መጥተውለት ፡ ለሥራ ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ሥራው ፡ ያለቀለት ፡ ሆስፒታል ፡ ለብዙ ፡ ሺህ ፡ ሕዝቦች ፡ ጤንነትና ፡ ደስታ ፡ ለመስጠት ፡ እንደሚረዳ ፡ ጸሎት ፡ እናደርጋለን ።

ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ ሆስፒታል ፡ ለመመረቅ ፡ ፈቃድዎ ፡ በመሆኑና ፡ ግርማዊነትዎና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትዎ ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ ለአደረጉልንና ፡ ለወደፊቱም ፡ ለሚያደርጉልን ፡ በጎ ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን ። አሁን ፡ አምባሳደራችን ፡ ክቡር ፡ ሸሪ ፡ ናራንጃን ፡ ሲንግኒል ፡ የዚህን ፡ ሆስፒታል ፡ መክፈቻ ፡ ቁልፍና ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በሚፈቅደው ፡ አኳኋን ፡ ለዚሁ ፡ ሆስፒታል ፡ ጥቅም ፡ የሚውል ፡ ዐሥር ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦርሳ ፡ ጭምር ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያቀብሉ ፡ ዘንድ ፡ በማክበር ፡ እጠይቃቸዋለሁ ።

* * *

ለ) የሕንድ ፡ አምባሳደር ፡ ንግግር ።

ግርማዊና ፡ ግርማዊት ፡
ልዑላን ፡
ክቡራንና ፡ ክቡራት ፡ ሆይ ።

በዚህ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ተግ ባር ፡ በማከናወን ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ። ሁላችሁ ፡ አሁን ፡ እን ደተረዳችሁት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚኖሩት ፡ የሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ ለኢት ዮጵያ ፡ ያላቸውን ፡ የምስጋና ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ ማስ ታወሻ ፡ ዛሬ ፡ ለዚች ፡ አገር ፡ ያበረክታሉ ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በዚህ ፡ በዓል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ በመገኘታቸው ፡ የክብር ፡ ስሜት ፡ ይሰጠናል ። ይህ ፡ ሆስፒታል ፡ የሕንድ ፡ ነጻነት ፡ አባት ፡ በሆኑት ፡ በማጎ ትማ ፡ ጋንዲ ፡ ስም ፡ በመሠየሙ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በሕንድና ፡ በኢት ዮጵያ ፡ መካከል ፡ ለሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ቀዋሚ ፡ ምልክት ፡ ይሆናል ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በውጭ ፡ አገሮች ፡ የሚኖሩ ፡ የሕንድ ፡ ተወላ ጆች ፡ ሁሉ ፡ ከሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ጥቅምና ፡ በጎ ፡ አኗኗር ፡ ጋር ፡ እንዲተሣሠሩ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትራችን ፡ ሽሪ ፡ ጀዋሀርላል ፡ ኔህሩ ፡ የሰጡትን ፡ ተገቢ ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ በመከተል ፡ የሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ ለዚች ፡ አገር ፡ (ኢትዮጵያ) የሚያደርጉላትን ፡ በጎ ፡ ተግባሮች ፡ እንዳላቋ ረጡ ፡ ዘወትር ፡ የሚያሳስብ ፡ ምሳሌ ፡ ይሆናል ።

ይህ ፡ ዛሬ ፡ ሥራው ፡ አልቆለት ፡ የሚታየው ፡ ሕንጻ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ በከተማው ፡ አማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ ባይሰጥ ፡ ኑሮ ፡ ከዚህ ፡ የሥራ ፡ ግብ ፡ ለመድ ረስ ፡ ፈጽሞ ፡ ባልተቻለም ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ይህ ፡ ሆስፒታል ፡ በማኅትማ ፡ ጋንዲ ፡ ስም ፡ እንዲሰየም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ራሳ ቸው ፡ ሐሳቡን ፡ አቅርበው ፡ እንዲሠራበት ፡ በመደረጉ ፡ ይህን ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ እስከ ፡ መቼም ፡ የምንረሳው ፡ አይደለም ። ይህ ፡ ሆስፒታል ፡ ለሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ተጨማሪ ፡ መልክና ፡ ግርማ ፡ በሰጠው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጀኔኛ ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥራው ፡ አልቆ ፡ አስፈላጊ ፡ መሣሪያዎች ፡ ደርሰውለት ፡ በመከፈቱ ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ።

የሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ባደረጉት ፡ ድካም ፡ ፍሬ ፡ ዛሬ ፡ ከመደሰታቸውም ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ የድካማቸው ፡ ፍሬ ፡ ለኢትዮጵያው ያን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጤንነትና ፡ ደስታ ፡ አገልግሎት ፡ ይውል ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አላቸው ። ከሕንድ ፡ ኮሙኒቴዎች ፡ አነስተኛ ፡ ሆኖ ፡ በቅን ፡ ልቡ

ና ፡ የቀረበውን ፡ የበጎ ፡ አስተያየት ፡ ስጦታ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ግርማዊነት ዎን ፡ በትሕትና ፡ እጠይቃለሁ ።

❋ ❋ ❋

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።
የሕንድ ፡ ኮሚዮኔቴ ፡ ፕሬዚዳን ።

የሕንድ ፡ ማኅበር ፡ ከነሙሉ ፡ ድርጅቱ ፡ ያበረከተውን ፡ ከታላቅ ፡ ስጦታ ፡ የምንቈጥረውን ፡ የዚህን ፡ ሆስፒታል ፡ ቍልፍ ፡ ስንቀበል ፡ በታ ላቅ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕይወት ፡ የሕንድ ፡ ማኅበር ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ የተከበሩትን ፡ የሕንድ ፡ አባት ፡ ማኅትማ ፡ ጋንዲን ፡ ክብር ፡ የያዘ ፡ በመሆኑ ፡ ይታገሉት ፡ ከነበረው ፡ ዓላማቸው ፡ ጋራ ፡ የተስ ማማ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሊኖረው ፡ ስለሚገባው ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ ታላቅ ፡ መሪ ፡ ለነበሩት ፡ ለማኅትማ ፡ ጋንዲ ፡ የክብር ፡ መታሰቢያ ፡ ማቆም ፡ እሳቸው ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ የደከሙበትንና ፡ በሰፊው ፡ የፈጸሙትን ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የተከበረውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊመራበት ፡ የተገባውን ፡ የተቀደሰ ፡ ምግባር ፡ ከመፈጸም ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

እናንተም ፡ ይህንን ፡ ሆስፒታል ፡ ለማቋቋም ፡ በማሰብ ፡ ሥራውን ፡ በማደራጀትና ፡ ከፍጻሜ ፡ በማድረስ ፡ ያላችሁን ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ለመፈ ጸም ፡ ከመቻላችሁ ፡ በላይ ፡ እውነተኛ ፡ የርኅራኄ ፡ አስተያየታችሁን ፡ ነዋሪና ፡ እርግጠኛ ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ገልጣችሁታል ።

በወንድማማችነት ፡ ለተሳሰሩት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ የመተሳሰብና ፡ የበጎ ፡ አስተያየት ፡ መልካም ፡ የሆነ ውን ፡ ይህን ፡ ለከተማችን ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ የሚአገለግለውን ፡ ሆስፒታል ፡ ከታላቅ ፡ ምስጋና ፡ ጋር ፡ ተቀብለናል ።

ይህን ፡ ሆስፒታል ፡ ለኢትዮጵያውያንና ፡ ለሕንዶች ፡ የሚያገለ ግል ፡ የማዋለጀ ፡ ሆስፒታል ፡ እንዲሆን ፡ ፈቅደናል ።

522

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዐድዋ ፡ ዐደባባይ ፡ ላይ ፡ ከጥሩ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራውን ፡ የአንበሳ ፡ ሐውልት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፸፮ ፡ ዓ.ም. በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ መርቀው ፡ ሐውልቱን ፡ ሲገልጹ ፡ የከተማው ፡ ገዢ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

ሀ) የከንቲባው ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ይህ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቲያትር ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሚገልጠው ፡ ከፍታ ፡ ቁመቱ ፡ ፲ ፡ ሜትር ፡ አግድመቱ ፡ ስምንት ፡ ሜትር ፡ የሆነው ፡ ከአገራችን ፡ ጥሩ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ የአንበሳ ፡ ሐውልት ፡ በአቀማመጡ ፡ የተለመደውን ፡ ደንበኛ ፡ አንበሳ ፡ መስሎ ፡ ባይታይም ፡ በመንፈስ ፡ አገላለጥ ፡ ጀግንነትን ፡ ኩራትን ፡ አለመናወጥን ፡ ተስፋ ፡ አለመቁረጥን ፡ ንቃትን ፡ በሙሉ ፡ ተገናጽፎአል ።

ይህ ፡ የአንበሳ ፡ አቀማመጥና ፡ ግርማ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሚልቶ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የሰጠው ፡ ዐይነታዊ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይና ፡ ባሕሪ ፡ ባምስቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የመከራ ፡ ዘመናት ፡ ዓለም ፡ የተገነዘበልዎትን ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ለመናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ እድገት ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽነትዎ ፡ ጀምሮ ፡ በሓያ ፡ አምስቱም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ላደረጉት ፡ ድካምና ፡ በተለይም ፡ ለአምስቱ ፡ ዓመት ፡ ትግልዎ ፡ ያልተረታ ፡ መንፈስዎን ፡ በማድነቅ ፡ ይህን ፡ ሐውልት ፡ ለሺኛው ፡ ዘውድ ፡ በዓልዎ ፡ መታሰቢያ ፡ ማበርከቱን ፡ ስገልጽ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

ከዚህም ፡ በማያያዝ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ዜጎችዎ ፡ አእምሮ ፡ ማጐልመሻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በጅምር ፡ ቀርቶ ፡ የነበረው ፡ የዚህ ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በሚመርቁበት ፡ ቀን ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ እንድናገር ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ ሕንፃ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ለሰሊማ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲሆን ፡ የታሰበ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪ ፡ ፈቅዶ ፡ ሥራውን ፡ ሲያስፈጽመው ፡ ለዘመናዊው ፡ ሲኒማ ፡ እስኮፕ ፡ ለቴያትር ፡ ለዳንስ ፡ ለሙዚቃ ፡ እንዲያገለግልና ፡ የተወደደው ፡ ሕዝብዎ ፡ ከነዚህ ፡ የሥልጣኔ ፡ መንግዶች ፡ በሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ እንዲጠቀም በትና ፡ ትምህርታዊ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በመስማት ፡ የመንፈሱ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ እንዲሄድ ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያገለግለው ፡ ስለፈቀደ ፡ ነው ።

ቴያትር ፡ ሙዚቃና ፡ ዳንስ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ኑሮ ፡ በሚሰጡት ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስካለንበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ተስፋፉና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ይዘው ፡ እንደሚገኙ ፡ ሁሉም ፡ የሚያውቀው ፡ በመሆኑ ፡ እዚህ ፡ ልዘረዝረው ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ አልታየኝም ።

ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ሦስቱ ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ አሁን ፡ ስናገር ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ተገኙ ፡ ለማሳሰብ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ የምንጫቸውን ፡ ክቡርነት ፡ እንድጠቅስ ፡ ይፈቀድልኝ ።

የማንኛውንም ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ብንመረምረው ፡ ሙዚቃ ፡ አጀማመሩ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ተግባሮች ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሙዚቃ ፡ አጣጣሉ ፡ እንደ ፡ ከዋክብትና ፡ እንደ ፡ ፕላኔቶች ፡ የመሰሉ ፡ የሰማይ ፡ አካላት ፡ የሚያደርጉትን ፡ መንቀሳቀስ ፡ ተከትሎ ፡ የሚሄድ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የሚያምኑበት ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ።

አርፌ ፡ የተባለው ፡ ጣዖታዊ ፡ አምላክ ፡ ክራር ፡ እየመታ ፡ በሚያሰማው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ እያገኙ ፡ እንዲመሰጡ ፡ አድርጎ ፡ ያጫውታቸው ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ በጥንት ፡ ጊዜ ፡ በነበሩት ፡ አረማውያን ፡ በሆኑት ፡ ግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ ይታመን ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ዳዊትም ፡ የሚበልጠው ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ በገና ፡ በመጫወት ፡ ነበር ።

ባገራችንም ፡ ያሬድ ፡ የደረሳቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ዜማዎችና ፡ ዝማሬዎች ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ሰጥተ

ውታል ። በሕዝባችን ፡ ዘንድ ፡ የሚገኙት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘፈኖችም ፡ የመ ጡት ፡ ከያሬድ ፡ ዜማዎች ፡ መንጭተው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የዜማን ፡ ታሪክ ፡ በሚመረምሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ይነገራል ።

በአውሮፓም ፡ እንደዚሁ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘው ፡ ሙዚቃና ፡ ዘፈን ፡ የተወሰደው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዜማ ፡ ነው ። ባዲሱ ፡ ዘመን ፡ የተነሡት ፡ ሙዚቀኞች ፡ እንደ ፡ ባክና ፡ እንደ ፡ ቤቶቨን ፡ አሁን ፡ በዘመ ናችን ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ቮጋን ፡ ዊልያምክና ፡ እንደ ፡ ስታራቪንስኪ ፡ የመ ሰሉት ፡ ሙዚቀኞች ፡ የተቀኙአቸው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ሙዚቃ ፡ ድርሰቶ ቻቸው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዜማ ፡ የመነጩ ፡ መሆናቸው ፡ ታውቋል ። ከሙዚቃ ፡ ጋራ ፡ በቅርብ ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ ዳንስ ፡ ወይም ፡ ጭፈራ ፡ አመጣጡ ፡ ከሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ። ለዚ ሁም ፡ ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እየሄደ ፡ በዜማ ፡ ሰክሮ ፡ ሲጨፍር ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተጽፎ ፡ የምናገኘው ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

"ድራማ" የተባለው ፡ የመጀሪያ ፡ ቴያትር ፡ ሥራ ፡ በጥንት ፡ ግሪ ኮች ፡ ዘንድ ፡ የተፈጠረው ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡ ይፈጽሙት ፡ ከነበረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሠረፀ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘት ፡ እንደሆነ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሙዚቃም ፡ ሆነ ፡ ዳንስ ፡ ቴያትርም ፡ የተገኘው ፡ ከተቀ ደሰ ፡ ስሜት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናል ።

በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ቴያትር ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሁኔታው ፡ ማረሚያ ፡ መስታወት ፡ የአእምሮው ፡ ማጐልመሻ ፡ ትምህ ርት ፡ መደሰቻውም ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ስለ ፡ ቴያትር ፡ ስናገር ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑት ፡ ሊቃውንት ፡ ከግሪኮች ፡ ኤሪፒድ ፡ ሶፎክልና ፡ አሪስቶፋን ፡ ከሮማውያን ፡ ሆራስ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ሼክስፒር ፡ ከጀርመን ፡ ገትና ፡ ሼለር ፡ ከፈረንሣይም ፡ የነ ፡ ኮርኔይ ፡ ራሲንና ፡ ሞሊዮርን ፡ ስም ፡ ሳልጠቅስ ፡ አላልፍም ።

ግርማዊነትዎ ፡ የአገርዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በትምህርት ፡ እንዲ ጐለምስ ፡ ካቀዱት ፡ ሰፊ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ቴያትርን ፡ ማበ ረታታት ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ በሰፊ ፡ ችሮታዎ ፡ ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የሰጡት ፡ ቴያትር ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፡ የፈጀውን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተ ለው ፡ እዘረዝራለሁ ።

፩ኛ ፡ ያለውን ፡ ሕንፃ ፡ አሻሽሎ ፡ ለመሥራት ፡ ከነወንበሮቹ ፡ ጭምር ፡	$640000
፪ኛ ፡ በራስ ፡ ሆቴል ፡ በኩል ፡ ቴራኩን ፡ ለማስፋፋት ፡ ዙሪያውን ፡ ምድር ቤት ፡ ወደፊት ፡ ለሱቅ ፡ እንዲያገለግል ፡ ለማድረግ ፡	$220000
፫ኛ ፡ በራስ ፡ ሆቴል ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ መተላለፊያ ፡ ጭምር ፡ ለማራዘም ፡	$ 68000
፬ኛ ፡ በአድዋ ፡ አደባባይ ፡ በኩል ፡ ላለው ፡ የቴያትር ፡ አደባባይና ፡ የውሃ ፡ ገንዳ ፡	$170000
፭ኛ ፡ ለሴኑ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ሞተርና ፡ ኢንስታላሲዮን ፡	$ 74420
፮ኛ ፡ ለሕንፃው ፡ ጌጣጌጥና ፡ ምንጣፍ ፡	$ 50314
፯ኛ ፡ ለታላቁ ፡ አንበሳና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐወልቶች ፡	$107000
፰ኛ ፡ ለቴያትሩ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ አምፑል ፡ መያዣዎች ፡ መስተዋቶች ፡ ለቡና ፡ ቤት ፡ ዕቃዎችና ፡ ወንበሮች ፡ ለሴኑ ፡ መኪናዎች ፡	$160000
፱ኛ ፡ ለአርቲስቶች ፡ ማረፊያ ፡ ክፍል ፡ ቤቶች ፡ ማደሻና ፡ ሙሉ ፡ ኢንስታላሲዮን ፡	$ 42688
፲ኛ ፡ በአድዋ ፡ አደባባይ ፡ ለተሠራው ፡ የውሃ ፡ ገንዳ ፡ ሐውልቶች ፡	$ 12000
፲፩ኛ ፡ ለቴያትሩ ፡ ቤት ፡ ዲኮራሲዮን ፡	$ 13000
፲፪ኛ ፡ ለአርቲስቶቹ ፡ ቤት ፡ ማጌጫ ፡ ለእኬስትር ፡ ቦታ ፡ ለሞዛይክ ፡ ሥራዎች ፡	$ 58429
፲፫ኛ ፡ ለሴኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሣሪያዎች ፡	$ 26000
፲፬ኛ ፡ ለናይት ፡ ክለብ ፡	$ 58149
በድምሩ ፡	$1700000

እንደሚፈጅ ፡ ታውቋል ።

ከዚህም ፡ ሒሳብ ፡ ናይት ፡ ክለቤ ፡ ወደፊት ፡ በሥርዓት ፡ የሚሠራ ፡ ነው ። ይህን ፡ ያህል ፡ ወጪ ፡ ያስጠየቀው ፡ ሕንፃ ፡ ለከተማው ፡ ውበት ፡ ሲሆነው ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ ለታማኙ ፡ ሕዝብዎ ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ እንደሚሰጥ ፡ የሁሉ ፡ ምኞት ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ ንግግሬን ፡ አሳጥራ ለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

523

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ገፈርሳ ፡ ላይ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ያሠራውን ፡ የውሃ ፡ ግድብ ፡ ጎዳር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፯፷፰ ፡ ዓ.ም. በ፲ ፡ ሰዓት ፡ መር ቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተ ሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ጃ ን ሆ ይ ።

ዛሬ ፡ የገፈርሣ ፡ ግድብና ፡ ማጣሪያ ፡ በሚመረቅበት ፡ ቀን ፡ ግርማዊ ነትዎና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ከልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጋር ፡ በቦ ታው ፡ ላይ ፡ ስለተገኙልን ፡ ለተሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ ሳልሰጠው ፡ የከተ ማውን ፡ ውሃ ፡ መሻሻል ፡ ሁኔታ ፡ ባጭሩ ፡ እንድናገር ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ።

ጃንሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ለተወዳጁ ፡ ሕዝብዎ ፡ በየጊዜው ፡ ካደረጉት ፡ ታላ ላቅ ፡ ሥራዎች ፡ በተለይ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሕይወትና ፡ ጠና ፡ የሆነው ፡ የውሃ ፡ ሁኔታ ፡ መሻሻል ፡ አንዱ ፡ ሲሆን ፡ ውሃ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ውሃ ፡ በእንዱስትሪ ፡ በእርሻ ፡ በአትክልት ፡ በርቢ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ በማገልገል ፡ ሲጠቅመው ፡ ይኖራል ። በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግ ሥት ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በተቆረቆረ ፡ ጊዜ ፡ በየቦታው ፡ ብዙ ፡ ምን ጮች ፡ ነበሩ ። በከተማው ፡ ሁኔታ ፡ መጠን ፡ ለዘመኑ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ውሃ ፡ እያለ ፡ በመቆየት ፡ የባሕር ፡ ዛፎች ፡ በብዛት ፡ በመተከላቸው ፡ ምክንያት ፡ እያደር ፡ ምንጮች ፡ እየደረቁና ፡ እንደዚሁም ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እየጨመረ ፡ በመሄዱ ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ ስላሠጋ ፡ ላንድ ፡ ከተማ ፡ ሕይወቱ ፡ ውሃ ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ከእንጦጦ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ፫ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ አስዘርግ ተው ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ ያካባቢው ፡ ሕዝብ ፡ ውሃ ፡ እንዲያገኝ ፡ አድ ርገው ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ መንበረ ፡ ክብር ፡ ከሚገኘው ፡ ምንጭ ፡ ባለ ፡ ፫ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ ስድስት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርዝመት ፡ ላይ ፡ አዘርግተው ፡ መናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡

አጠገብ ፡ ካለው ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ገብቶ ፡ ለመሐል ፡ ከተማ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲታደል ፡ አድርገው ፡ ይህም ፡ አልበቃ ፡ ስላለ ፡ ከእንጦጦ ፡ በ፲፪ ፡ ኪሎ፡ ሜትር ፡ ርዝመት ፡ በባለ ፡ ፫ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ ውሃ ፡ አስመጥተው ፡ በመ ስፍን ፡ ሐረር ፡ መንገድ ፡ መነሻ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጐዳና ፡ ከዳ ግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አደባባይ ፡ እስከ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ድል ድይ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በንጹሕ ፡ ውሃ ፡ ሲጠቀም ፡ ቆይቷል ።

ጠላትም ፡ አገራችንን ፡ በወረረ ፡ ዘመን ፡ ከኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ምንጭና፡ ከቀበና ፡ ሁለት ፡ ረድፍ ፡ ባለ ፡ ፬ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ በ፬ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርዝመት ፡ ዘርግቶ ፡ በእንጦጦ ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ማጠራቀሚያና ፡ ማጣሪያ ፡ ሠርቶ ፡ እንደዚሁ ፡ ከአዲስ ፡ ዓለም ፡ መንገድ ፡ ኮንሌ ፡ ከሚባ ለው ፡ ሥፍራ ፡ ፮ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ባለ ፡ ፬ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ በዘረጋም ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማን ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ ሁኔታ ፡ ጨርሶ ፡ ለማስወገድ ፡ አልቻ ለም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ በየጊዜው ፡ በሚ ሰጠው ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ፮ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ባለ ፡ ፫ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ በመዘርጋት ፡ በአዲስ ፡ ዓለም ፡ መንገድ ፡ ከሚገኘው ፡ ምንጭ ፡ ጠልፎ ፡ በማስገባት ፡ ከትንሹ ፡ ቀበና ፡ ፩ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ በባለ ፡ ፫ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ በማስመጣት ፡ በኡራኤል ፡ የካ፡ ራስ ፡ ብሩ ፡ ሰፈር ፡ የሚገኙትን ፡ ሕዝቦች ፡ ችግር ፡ ለማስታገሥ ፡ ተች ሏል ።

የገፈርሳን ፡ ግድብ ፡ ቧንቧ ፡ ምንም ፡ ጠላት ፡ ቢጀምረው ፡ በ፮ ፡ ኪሎ ሜትር ፡ ርዝመት ፡ ባለ ፡ ፮ ፡ ኢንች ፡ ቧንቧ ፡ በመዘርጋትና ፡ በየሥፍራ ውም ፡ ፴ ፡ ጥልቅ ፡ ጕድጓዶች ፡ በማስቆፈር ፡ በሞላ ፡ ጎደል ፡ ለከተማው ፡ ውሃ ፡ አበርክቶ ፡ ለመስጠት ፡ ተደክሟል ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ከየሥፍራው ፡ በቀን ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ የሚገባው ፡ የውሃ ፡ ብዛት ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ ከገፈርሳ ፡ 2500 ሜትር ፡ ኩብ
፪ኛ ፡ ከእንጦጦ ፡ 1200 ” ”
፫ኛ ፡ ከጉለሌ ፡ ምንጭ ፡ 500 ” ”

፬ኛ ፡ ከመስፍን ፡ ሐረር ፡ መንገድ ፡ ምንጭ ፡ 250ሜትር ፡ ኩብ
፭ኛ ፡ ከትንሹ ፡ ቀበና ፡ 300 ፡፡ ፡፡
፮ኛ ፡ ከመንበረ ፡ ክብር ፡ 200 ፡፡ ፡፡
፯ኛ ፡ ከጉድጓዶች ፡ 450 ፡፡ ፡፡
፰ኛ ፡ ለምድር ፡ ባቡር ፡ ኩባንያ ፡ ከወጨጫ ፡ የሚመጣው ፡ 300 ፡፡ ፡፡
ድምር ፡ 5700 ፡፡ ፡፡

ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እየቀጠለ ፡ እንደመ ሄዱ ፡ መጠን ፡ የሚበቃ ፡ ውሃ ፡ አላገኘም ፡ ዘወትር ፡ የሕዝብዎን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ የሚደክሙ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በተለመደው ፡ ታላቅ ፡ ችሮ ታዎ ፡ ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ባደረጉት ፡ ሰፊ ፡ እርዳታ ፡ ግድቡ ፡ የስድስት ፡ ሜትር ፡ ከፍታ ፡ አግኝቶ ፡ የበቃ ፡ ውሃ ፡ እንዲያከማች ፡ ማጣሪ ያውንም ፡ በዘመናዊ ፡ አቅድ ፡ ለመሥራት ፡ ባለ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሚሊ ፡ ሜትር ፡ ዲያሜትር ፡ ቧንቧ ፡ በ፲፫ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርዝመት ፡ ዘርግቶ ፡ በመስፍን ፡ ሐረር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ለጋስነት ፡ ከተሠራው ፡ ፲ሺህ ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ ከሚይዘው ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ለማገናኘት ፡ $3477.000 ወጪ ፡ ሆኗል ። የወጪውም ፡ ዝርዝር ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ለግድቡ ፡ $1.500.000
ለማጣሪያ ፡ ሕንፃና ፡ መኪናዎች ፡ 800.000
ለቧንቧ ፡ 680.000
በመስፍን ፡ ሐረር ፡ መንገድ ፡ ላለው ፡ ማጠራቀሚያ ፡ 497.000
ድምር ፡ $3.477.000
ግድቡ ፡ በጠቅላላው 600.000 ሜትር ኩብ ፡ ሲይዝ ፡ ማጣሪያው ፡ በቀን ፡ ፲፭ሺህ ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ ንጹሕ ፡ ውሃ ፡ ይሰጠናል ።

በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የከተማው ፡ ነዋሪ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በቀን ፡ ፶ ፡ ሊትር ፡ ውሃ ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችል ፡ ተገምቷል ። ፴ሺህ ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ ንጹሕ ፡ ውሃ ፡ ለማደል ፡ አሁን ፡ ካለው ፡ ማጣሪያ ፡ ጐን ፡ ወደፊት ፡ ሌላ ፡ ማጣሪያ ፡ ለመሥራት ፡ ታቅዷል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለአንዳንድ ፡ ሰው ፡

100 ሊትር ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

ከገፈርሳ ፡ የሚገኘው ፡ ውሃ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ላንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ በቂ ፡ መሆኑ ፡ በመሐንዲሶች ፡ ተጠንቶ ፡ የተረጋገጠ ፡ ቢሆንም ፡ ለወደፊቱ ፡ ሕዝቡን ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ እንዳያገኘው ፡ በማሰብ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ካሁን ፡ ጀምሮ ፡ በሰፊ ፡ ጥናት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህንኑ ፡ ግድብና ፡ የውሃ ፡ ማጣሪያ ፡ በጥንቃቄ ፡ ላከናወኑት ፡ ለዲኤ ግራም ፡ ኩባንያ ፡ ዲሬክተርና ፡ መሐንዲሶች ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ምስ ጋና ፡ እንዳቀርብላቸው ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስለምን ፡ ለመናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ሕዝብ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለሕይወቱ ፡ ሆነ ፡ ለጤ ናው ፡ አስፈላጊው ፡ የሆነውን ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ ስላስወገዱለት ፡ ውለታ ፡ መላሽነቱን ፡ ከዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ እገልጻለሁ ።

ፅድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ፅድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ፅድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ከሰው ፡ ሕይወትና ፡ ኑሮ ፡ ጋራ ፡ የተሳሰሩትን ፡ የውሃና ፡ የብርሃን ፡ አስፈላጊነት ፡ በማወቅ ፡ እያደገ ፡ የሚሄደው ፡ የከተማችን ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ያለበትን ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ አስበን ፡ ካቀድነው ፡ ፕሳ ናችን ፡ አንዱ ፡ ዛሬ ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ተፈጽሞ ፡ በማየታችን ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

ይህን ፡ ሥራ ፡ በቴክኒክ ፡ ረገድ ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የደከሙ ትን ፡ የዲኤግራምን ፡ ኩባንያ ፡ መሐንዲሶች ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

እንዲሁም ፡ ሥራውን ፡ በቅርብ ፡ እየተከታተሉ ፡ ትእዛዛችንን ፡ ያስ ፈጸሙት ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ባሳዩት ፡ ትጋትና ፡ ብርታት ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

524

የእስፓኝ ፡ ሬፕብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስትር ፡ ገቢ ፡ ቢልካስታኖ ፡ ጎዳር ፡ ፪ ቀን ፡ ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ በጎነት ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ክቡር ፡ የእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ መሪ ፡ ጄኔራሊስሞ ፡ ፍራንኮ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ የተሾምኩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ለኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ነው ።

በኢትዮጵያና ፡ በእስፓኝ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ግንኙነት ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ እንዳከናውን ፡ መንግሥቴ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እምነት ፡ ስለጣለብኝ፡ ዕድለኛ ፡ ነኝ ።

እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ አስቸጋሪ ፡ ምክንያት ፡ ገጥሟቸው ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በታሪኮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ያገር ፡ ወዳድነት ፡ ተግባር ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ ችለዋል ።

ከእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ መሪ ፡ ከክቡር ፡ ጄኔራሊስሞ ፡ ፍራንኮ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ደኅንነት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ልማት ፡ በመመኘት ፡ የተነገረኝን ፡ መልክት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

ይህንን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜና ፡ እንዲሁም ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ ፍቅር ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማደርገው ፡ ድካም ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባቂነትና፡ የመንግሥቱ ፡ እርዳታ ፡ እንዳይለየኝ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትሕትና ፡ አሳስባለሁ ።

ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ደኅንነትና ፡ ጸጋ ፡ ያለኝን፡ ምኞት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስገልጽ ፡ እንዲሁም ፡ ግርማዊነትዎ፡ በነገሡበት ፡ በሸኟኛ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የተከናወኑትን ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ሥራዎችና ፡ እንዲሁም ፡ የሚቀጥሉትን ፡ አስደናቂ ፡ ተግባሮች ፡ ለግርማዊነትዎ፡

እንድገልጽ ፡ ንግግሬን ፡ ከመፈጸሜ ፡ በፊት ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ። እንዲሁም ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤዬን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ እጅ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር፡ እየተሰማኝ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ የእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ከክቡር ፡ የእስፓኝ ፡ መሪ፡ ከጄኔራሊስሞ ፡ ፍራንኮ ፡ የተሰጠዎትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

በኢትዮጵያና ፡ በእስፓኝ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መልካም ፡ ወዳጅነት፡ የበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ በሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ እንደማይለይዎ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ። ለተላኩበትም ፡ ከፍተኛ ፡ መልክት ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እርዳታና ፡ መተባበር ፡ አይጓደልብዎትም ።

በእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ በክቡር ፡ ጄኔራሊስሞ ፡ ፍራንኮ ፡ ስም ፡ ስለአቀረቡልን ፡ ሰላምታና ፡ ስለ ፡ ገለጡልንም ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፡ በኛም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የወዳጅነት ፡ ስሜትና ፡ ሰላምታ ፡ እንዲያደርሱልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

525

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ጀኟኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አያቢልዩ ፡ ክብር ፡ ጎዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማታ ፡ በግዮን ፡ ሆቴል ፡ ባደረገው ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ፡ የከተማው ፡ ገዢ ፡ ክቡር ፡ ክንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ክንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

በታላቅ ፡ ናፍቆት ፡ እንጠባበቀው ፡ የነበረው ፡ የሸፍኛ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ደርሶ ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ካዘጋጀነው ፡ እራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌና ፡ ከልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጋር ፡ ስለተገኙልን ፡ በተወዳጁ ፡ በከተማዎ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ የተሰማኝን ፡ ደስታ ፡ እንድገልጽ ፡ ይፈቅዱልኝ ዘንድ ፡ አስቀድሜ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በታሪክ ፡ እንደተመለከትነው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ ደጋግ ፡ መሪዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ከቶ ፡ እንደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ላንድ ፡ ፍጡር ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነው ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮበት ፡ በሁሉም ፡ የተሟላ ፡ ዕድል ፡ ያገኘ ፡ የለም ። እንዲህም ፡ ማለቴ ፡ ሌሎቹን ፡ በመንቀፍ ፡ ሳይሆን ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መጨረሻ ፡ ተስፋው ፡ ነፃነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከባዱን ፡ መከራ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብዎ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ሊያስወግዱለት ፡ የቻሉ ፡ ጃንሆይ ፡ ብቻ ፡ ነዎት ፡ ማለቴ ፡ ነው ።

ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ አገሮች ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ እየወደቁ ፡ ዋንትም ፡ ሆነ ፡ ዛሬም ፡ በኛው ፡ ዘመን ፡ ታይተዋል ። አንዳንዶቹ ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለማስመለስ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ሲአስፈልጋቸው ፡ ማናቸውም ፡ ደግሞ ፡ ከ፶ ፡ ዓመት ፡ ባነሰ ፡ ዘመን ፡ የመገዛት ፡ ቀንበራቸውን ፡ ያወረዱ ፡ አይገኙም ።

ስለዚህ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብዎ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ የሸፍኛውን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ሲያከብር ፡ የሚሰማው ፡ ስሜት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የሚያደርገው ፡ የደስታ ፡ መግለጫው ፡ የማይበቃው ፡ መስሎ ፡ ስለሚታየውና ፡ የሚበቃም ፡ ቃል ፡ ስለማይገኝለት ፡ ለዚሁ ፡ ደስታው ፡ መጨመሪያ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ ይህንን ፡ ግብዣ ፡ በትሕትና ፡ አዘጋጀ ።

በዚሁ ፡ ግብዣው ፡ ስለተገኙልን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናዬን ፡ ሳቀርብ ፡ እንዲሁም ፡ የወርቅ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በዓልዎን ፡ ለማክበር ፡ እንዲያበቃው ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንዲጠብቅለት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብዎ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ምኞቴን ፡ በትሕትና ፡ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በሸፍኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓላችን ፡ ምክንያት ፡ በመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ በተዘጋጀው ፡ ግብዣ ፡ ለመገኘት ፡ ስንመጣ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

የተወደደው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ሕዝባችን ፡ በየጊዜው ፡ ምክንያት ፡ ባጋጠመው ፡ ቊጥር ፡ የሚያደርግልን ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ከልብ ፡ ይሰማናል ።

ዛሬም ፡ እንደዚሁ ፡ የደስታችን ፡ ተካፋይ ፡ በመሆኑ ፡ ያደረገልን ፡ አቀባበል ፡ ከልባችን ፡ አይጠፋም ።

526

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሸፍኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቢልዩን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ማደሪያ ፡ መሬትና ፡ ስለ ፡ ባንክ ፡ መቋቋም ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ ምሕረትና ፡ ቅጣትን ፡ ስለመቀነስ ፡ ጎዳር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያስነገሩት ፡ የአዋጅ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ የወጣ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ።

ሀ) የአዋጁ ፡ ቃል ።

ሞኣ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዋጅ ።

ለሕዝባችን ፡ ደኅንነት ፡ ለኑሮው ፡ ብልጥግናና ፡ ልማት ፡ የምናስብበት ፡ ተግባራችን ፡ ስለሆነ ፡ እርሻህን ፡ እንድታለማ ፡ ንግድህን ፡ እንድታስፋፋ ፡ ዛሬ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ በጫንበት ፡ በሸፍኛው ፡ ኢዮቤ

ልዩ ፡ በዓላችን ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አዘንልሃል ።

፩ኛ፡ የማደሪያ ፡ መሬት ፡ ያለህ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከአንዱ ፡ ጋሻ ፡ ሚሦው ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ ርስት ፡ እንዲሆንልህ ፡ በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፈቅደንልህ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በማደሪያነት ፡ በያዝከው ፡ በቀሪው ፡ በሁለቱም ፡ እጅ ፡ መሬት ፡ የወር፡ ተራ ፡ ዘብ ፡ ጥበቃ ፡ ሥራ ፡ ትሠራበት ፡ የነበረውን ፡ አስቀርተን ፡ ሁለቱም፡ እጅ ፡ መሬት ፡ ተጨምሮ ፡ አንዱ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ በሙሉ ፡ ርስት ፡ እንዲሆንልህ ፡ ፈቅደንልሃል ። ከአንድ ፡ ጋሻ ፡ ያነሰም ፡ የያዝክ ፡ ሰው ፡ ያው ፡ የያዝከው ፡ በሙሉ ፡ ርስት ፡ እንዲሆንልህ ፡ ፈቅደናል ። የዚህንም ፡ የፈቀድንልህን ፡ መሬት ፡ ሙሉ ፡ ግብር ፡ ከ፲፱፻፺፱ ፡ ዓ.ም. ጀምሮ ፡ እንድትከፍልበት፡ አድርገንልሃል ።

ይህንንም ፡ ሰላደረግንልህ ፡ ቀድሞ ፡ ትሠራ ፡ የነበረውን ፡ የዘብ ፡ ጥበቃ ፡ ሥራ ፡ በምትሠራበት ፡ ወራት ፡ ደሞዝ ፡ እየተቀበልህ ፡ ደንበኛ ፡ ፖሊስ ፡ በሚገባ ፡ ተቋቁሞ ፡ እስኪተካልህ ፡ ድረስ ፡ እየሠራህ ፡ እንድትቆይ ። ለዚህም ፡ ለምትሠራበት ፡ ወራት ፡ የምትቀበለውን ፡ ደምዝ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ እንዲያስፈጽምልህ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴራችንን ፡ አዘንልሃል።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በርስትነት ፡ የፈቀድንልህን ፡ መሬት ፡ በመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ ለማስገቢያ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ እየከፈልህ ፡ ባለርስትነትህን፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንድታጽፍ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርንና ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርን ፡ አዘንልሃል ።

፪ኛ፡ ንብረትህን ፡ ለማደርጀት ፡ ንግድህን ፡ ለማስፋፋት ፡ ከመንግሥታችን ፡ ባንክ ፡ አስቀድሞ ፡ ለተበደርከውና ፡ ወደፊትም ፡ ለምትበደረው፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ወለዱ ፡ እንዲቀነስልህ ፡ ደግሞም ፡ አሁን ፡ ካለው ፡ ከመንግሥታችን ፡ ባንክ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ ባንኮች ፡ ተቋቁመው ፡ እንዲሠሩ ፡ አዘንልሃል ።

፫ኛ፡ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ በፊትና ፡ ጠላትም ፡ አገራችንን ፡ ይዞ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡

ሀ) እርስ ፡ በርስ ፡ በመገዳደል ፡ ምክንያት ፡ ተፈርዶብህ ፡ ወይም ፡ ተከሰህ ፡ ገና ፡ ሳይፈረድብህ ፡ በውህኒ ፡ ቤት ፡ የምትገኝ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ወንጀል ፡ እስካሁን ፡ ያልተከሰስህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁሉ ፡ ምረንሃል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶብህ ፡ በዚህ ፡ የምሕረት ፡ አዋጅ ፡ የምትለቀቅ ፡ ወንጀለኛ ፡ ከባለደሙ ፡ ጋራ ፡ ካልተስማማህ ፡ በቀር ፡ ነፍስ ፡ ባጠፋህበት ፡ ወረዳ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ወረዳ ፡ መኖር ፡ አለብህ ።

ለ) ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ በማቃጠል ፡ ገንዘብ ፡ በመዘራረፍ ፡ በሌላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ምክንያት ፡ ተፈርዶብህ ፡ ወይም ፡ ተከሰህ ፡ ገና ፡ ሳይፈረድብህ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ የምትገኝ ፡ ወይም ፡ እስካሁን ፡ ሳትከሰስም ፡ ሳይፈረድብህም ፡ የምትገኝ ፡ ሁሉ ፡ በመንግሥታችን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ቅጣት ፡ ምረንሃል ።

፬ኛ ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ቤት በማቃጠል ፡ ገንዘብ ፡ በመዝረፍ ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ወንጀል ፡ ተከሰህ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ ተፈርዶብህ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ የምትገኝ ፡ የዕድሜ ፡ ልኩን ፡ እስራት ፡ በሓያ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ለውጠንልሃል ። ይኸውም ፡ ከታሰርክበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ይቈጠራል ።

፭ኛ፡ በጥፋተኛነት ፡ ተፈርዶብህ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ላለህ ፡ እስረኛ ፡

ሀ) ከአንድ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሆነ ፡ የእስራት ፡ ፍርድ ፡ ላለበት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡

ለ) ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ላለበት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡

ሐ) ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ላለበት ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እንዲቀ

፮ኛ፡ የመሬት ፡ ግብርና ፡ ሌላም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ታክስና ፡ ቀረጥ ፡ ውዝፍ ፡ ያለብህ ፡ ልትከፍለው ፡ የሚገባህን ፡ ዋናውን ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፺፰ ፡ ዓ.ም. መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የከፈልክ ፡ እንደሆነ ፡ በመቀጫ ፡ ምክንያት ፡ ይጨመርብህ ፡ የነበረውን ፡ ዕዳ ፡ ምረንሃል ።

❋ ❋ ❋

ለ/ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ለአገራችን ፡ ልማትና ፡ ለሕዝባችን ፡ እድገት ፡ ጠቃሚነቱ ፡ የታወቀው ፡ ትምህርት ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በበለጠ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ማስፈ

ለጉን ፡ ተመልክተን ፡ ይህም ፡ መስፋፋት ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝ ባችን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጎዳና ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለትምህርት ፡ ታክስ ፡ አከፋፈል ፡ በወጣው ፡ በቀጥር ፡ ፭፩ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከሚከፍለው ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ ታክስ ፡ ሌላ ፡ ራሱ ፡ የሚጠቀም በት ፡ ትምህርት ፡ በበለጠ ፡ እንዲረዳ ፡ አስበን ፡

የትምህርት ፡ አገልግሎት ፡ በየዘመኑ ፡ የሕዝቦችን ፡ ባህል ፡ በማሻ ሻልና ፡ የኑሮአቸውን ፡ ደረጃ ፡ በማሳደግ ፡ የሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ከፍተኛ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ እንደዚሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የአማርኛን ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተን ፡ በጠቅላላው ፡ ለሥጋዊም ፡ ሆነ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሕይወት ፡ መንገድ ፡ ከፋቺ ፡ ለአገርና ፡ ለነፃነት ፡ ጥ በቃ ፡ ዋናው ፡ መሣሪያ ፡ ትምህርት ፡ መሆኑን ፡ ተረድተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ውን ፡ አዘናል ።

፩፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ‘‘መሠረተ ፡ ትምህርት ፡’’ ለሁሉ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ስለመግለጽ ፡ የወጣ ፡ የ፲፱፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማስታወቂያ ፡ ተብሎ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪፡ በዚህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ ‘‘ወጣት ፡’’ ማለት ፡ በሰባትና ፡ በአሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ ልጅ ፡ ማለት፡ ነው ። ‘‘መሃይምን ፡ ማለት ፡ ’’ለመሠረተ ፡ ትምህርት ፡ የተመደበውን ፡ ትምህርት ፡ ያልተማረ ፡ ወይም ፡ ለማንበብና ፡ ለመጻፍ ፡ ያልቻለ ፡ ማለት፡ ነው ።

‘‘መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ’’ማለት ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ከፊደል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማንበብና ፡ እስከ ፡ መጻፍ ፡ ድረስ ፡ ሆኖ ፡ የተመደበ ፡ የት ምህርት ፡ ክፍል ፡ ነው ።

‘‘አስተዳዳሪ ፡ ’’ማለት ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚያስተዳድር፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ቃል ፡ የሞያ ፡ ሠራተኞችን ፡ የሚያሰራውን ፡ ሰው ፡ አይጨ ምርም ። ‘‘ሚኒስቴራችን ፡ ’’ማለት ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒ ስቴር ፡ ማለት ፡ ነው ። ‘‘የግል ፡ አስተማሪ ፡ ’’ማለት ፡ መሠረተ ፡ ትምህ ርትን ፡ ለማስተማር ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይህንኑ ፡ ተግባር ፡ አድ ርጎ ፡ የሚሠራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ ፡ ሀ) ወጣቶች ፡ ሁሉ ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ የመጀመሪያውን ፡

ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ለ) ወላጆች ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ ለመጠበቅና ፡ ለማሳደግ ፡ ተግባር ፡ ያለባቸው ፡ ማናቸውም ፡ ሰዎች ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከሰባት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ የሆኑትን ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የመጀመሪያውን፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

ሐ) በመንግሥት ፡ የተቋቋሙ ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ትምህርትን ፡ በነፃ ፡ እንዲሰጡ ፡ አድርገናል ።

፬) በዚህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ የተመለከተው ፡ ሳይቀር ፡ በ፲፰ና ፡ በ፵ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ መሃይምን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ከዕለት ፡ ተግባሩ ፡ በሚተርፈው ፡ ሰዓት ፡ በአቅራ ቢያው ፡ በሚገኝ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም፡ በየመንደሩና ፡ በየቀበሌው ፡ የግል ፡ አስተማሪ ፡ እየቀጠረ ፡ የአማርኛን፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችለውን ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማር ፡ አደራ ፡ ጥለንበታል ።

527

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለሟቿኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አድቤልዩ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ኤግዚቪሽን ፡ ጎዳር ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸ ፡ ዓ፡ም፡ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲጐበኙ ፡ የጉራጌ ፡ ሕዝብ ፡ በአንድ ፡ ድርጅት ፡ አማካይነት ፡ እንደ ፡ አገሩ፡ ባህል ፡ ያዘጋጃቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ዕቃዎች ፡ ከተመለከቱ፡በኋላ፡የድርጅቱ፡ፕሬዚዳንት ፡ አቶ ፡ አል ፍሬድ ፡ ሻፊ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የአቶ ፡ አልፍሬድ ፡ ሻፊ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በጥ ንቃቄ ፡ ጠብቆ ፡ ለሟቿኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ያደረሰዎ ፡ አምላክ ፡ ይክበር፡ ይመስገን ።

ጃንሆይ ።

ይህን ፡ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነውን ፡ ትሑት ፡ ሥራችንን ፡ ሊጐ በኙልን ፡ ፈቅደው ፡ በመምጣትዎ ፡ ባጋጠመው ፡ ዕድል ፡ የጉራጌ ፡ ሕዝብዎ፡

ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊነገር ፡ የማይቻል ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰማዋል ።

ይህ ፡ የጉራጌ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፰፩፰ው ፡ የዘውድ ፡ በዓልዎ ፡ ክብር ፡ በተ ዘጋጀው ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ትርእይት ፡ መካከል ፡ ለመገኘት ፡ የቻለው ፡ ቀዋሎ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ሐሳቡን ፡ የወጠነችው ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ገድብ ፡ ሆና ፡ ጉዳዩም ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንዲደርስላት ፡ እስከ ፡ ማድረግ ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ደከመ ችበት ። ግርማዊነትዎም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ከሚያ ስቡበት ፡ ዋነኛው ፡ አንዱ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ የተግባረ ፡ እድ ፡ እርምጃ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የዚህም ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ትርእይት ፡ መካከል ፡ መገ ኘት ፡ የሐሳቡን ፡ ታላቅነት ፡ ተመልክቶ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አስተያየት ፡ ስለተቀ በለው ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ቤቱ ፡ ተሠርቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ቦታና ፡ ለሥራውም ፡ ያስፈለገውን ፡ ዕቃ ፡ ማምጫ ፡ ካሚዮን ፡ በነፃ ፡ እንድናገኝ ፡ ሰፊ ፡ ልግሥና፡ አደረገልን ።

ሥራውን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚችል ፡ በሀገሬው ፡ ዘንድ ፡ ተፈቃሪና ፡ ተደማጭ ፡ የሆነ ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ ማስፈለጉ ፡ ተጠንቶ ፡ ምርጫው ፡ በቃ ጥባሬው ፡ ሼህ ፡ ልጅ ፡ በሻምበል ፡ ሡልጣን ፡ ኢሳ ፡ ላይ ፡ ወረፈ ። እርሱም፡ የተመረጠበትን ፡ አገልግሎት ፡ አላንዳች ፡ ማመንታት ፡ ተቀብሎ ፡ ለቤቶ ች ፡ አሠራር ፡ ያስፈለጉትን ፡ ዕቃዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ ለማምጣት ፡ በጭለ ማው ፡ ክረምት ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ቤት ፡ ሄደ ። ዕቃውንና ፡ መሣ ሪያውን ፡ የበኩሉን ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ አዘጋጅቶ ፡ የሀገር ፡ ቤቱን ፡ ሕዝብ ፡ ሴት ፡ ተወንድ ፡ ሳይለይ ፡ ዕቃውን ፡ በማቅረብና ፡ ተሠርቶ ፡ መገኘት ፡ የነ በረበትንም ፡ እዚያው ፡ በመፈጸም ፡ ከወንዝ ፡ ወንዝ ፡ በማቀባበል ፡ እስከ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ አደረስንለት ። ስለ ፡ ቤቱም ፡ አሠራር ፡ ዕውቀት ፡ ያላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ የአዝመራቸውን ፡ ጊዜ ፡ መሥዋዕት ፡ በማድረግ ፡ ቤት ፡ ንብረታቸውንም ፡ ጥለው ፡ መጡ ።

ቤቱ ፡ በመላው ፡ ጉራጌ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራ ፡ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ እንደሚሰጥ ፡ አስቀድሞ ፡ ታስቦበት ፡ ቆይቶ ፡ ስለነበረ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚኖሩ ፡ የጉራጌ ፡ ተወላጆች ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ ጥሪ ፡ ተደረገ ፡ ለነ ርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ የተወጠነ ፡ ነገር ፡ ማሳየት ፡ የሚሻል ፡ መሆኑ ፡ ተጠ ንቶ ፡ ዕቃውና ፡ ሠራተኞቹ ፡ እንደመጡ ፡ የቤቱ ፡ ሥራ ፡ ተጀምሮ ፡ በማየ

ታቸው ፡ ሐሳብም ፡ ተገልጾላቸው ፡ ተደሰቱበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሥ ራው ፡ እየቀጠለ ፡ ከከተማው ፡ ነዋሪ ፡ የጉራጌ ፡ ሕዝብ ፡ ሽማግሌው ፡ ከጐ ልማሳው ፡ ሴት ፡ ከወንዱ ፡ ሀብታም ፡ ከድሃው ፡ ሳይለይ ፡ ተሰብስቦ ፡ አ ንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ እኔ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኜበታ ለሁ ፡ እያለ ፡ በዕውቀቱ ፡ በገንዘቡና ፡ በጉልበቱ ፡ እየተረዳዳ ፡ ባደረገው ፡ ጥረት ፡ እነሆ ፡ ይህን ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሊጐበኙልን ፡ ክብር ፡ ያገኘ ውን ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ ተቻለ ።

ጃንሆይ ።

ይህን ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ትርእይት ፡ መካከል ፡ ሠርቶ ፡ ለማሳየት፡ ከጉራጌ ፡ ሕዝብዎ ፡ የከተማውም ፡ የባላገሩም ፡ እስከዚህ ፡ የተባበረበት ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ቁም ፡ ነገሮችን ፡ ያስገኛል ፡ በሚል ፡ ግምት ፡ ተደግፎ ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ ቁም ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ የጉራጌ ፡ ቤት አንዳች ፡ የተውሶ ፡ ዕቃና ፡ ሥራ ፡ ምስማር ፡ ስንኳ ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተግባር ፡ እንደመሆኑ ፡ በዚህ ፡ ትርእይት ፡ መካከል ፡ ሲገኝ፡ ስለቀረውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የባላገር ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ለመቅረብና፡ አንዱም ፡ ደግሞ ፡ የእርሱን ፡ ያህል ፡ ቀጥ ፡ በማይታይባቸው ፡ በአንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የባላገር ፡ ቤቶች ፡ በአመራር ፡ ዐቅድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ፡ እንዲያገለግል ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ በመመኘት ፡ ሐሳብ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በረኻሙ ፡ ዘመን ፡ መንግሥትዎ ፡ በመሪነትዎ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ በር ኅራኄም ፡ እንደ ፡ እናት ፡ ሆነው ፡ ስለሕዝብዎ ፡ እድገት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ያደረጉትና ፡ የሚደርጉት ፡ ጥረት ፡ ካስገኘው ፡ ፍሬ ፡ ድርሻውን ፡ የታደ ለው ፡ የጉራጌ ፡ ሕዝብዎ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያለበትን ፡ ው ለታ ፡ ለመክፈል ፡ በሕሊና ፡ የሚገደድበት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ የውለታውን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ማቅረብ ፡ ሲኖርበት ፡ እላይ ፡ እንደተነገረው ፡ ሁሉ ፡ የከተማው ፡ ከባላገሩ ፡ ሴት ፡ ከወንዱ ፡ ሽማግሌ ፡ ከጐልማሳው ፡ ሀብታም ፡ ከድሃው ፡ ሳይለይ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ፍቅር ፡ አስተሳስሮት ፡ በዕውቀቱ ፡ በገንዘቡና ፡ በጉልበቱ ፡ ተባብሮበት ፡ የሠራ ውን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ማበርከት ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለ ፡ መሆ

ኑን ፡ ስለገመተው ፡ በዋጋው ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ግምቱ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሊበረከት ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ አለመሆኑንም ፡ እያወቀ ፡ ስለግርማዊነትዎ ፡ ፍቅር ፡ ሲል ፡ የተባበረበት ፡ ዓላማው ፡ አመዝኖ ፡ እግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ የመቀበል ፡ ሞገስ ፡ እንዲያገኝ ፡ ልመናውን ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ አሠራር ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ስለሚገኘው ፡ የአኗኗሩን ፡ ሥርዓት ፡ ለመግለጫ ፡ ያህል ፡ ካዘጋጀው ፡ ጽሑፍ ፡ ጭምር ፡ በታላቅ ፡ ፍርሃት ፡ እያቀረበ ፡ እንደዚሁ ፡ አምላክ ፡ በዓለም ፡ በጤና ፡ ጠብቆ ፡ ለሟኘው ፡ የዘውድ ፡ በዓልዎ ፡ እንዲያደርስዎ ፡ ምኞቱን ፡ ይገልጻል ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡

ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡እቴጌ ፡

ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የጉራጌ ፡ ሕዝብ ፡ በታላቅነትና ፡ ስለሀገሩም ፡ ክብር ፡ ደሙን ፡ በማፍሰስ ፡ እንዳልቦዘነ ፡ ማንም ፡ አይዘነጋውም ፡ በኤኮኖሚና ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ፡ ድካም ፡ ሳይሰማችሁ ፡ በምታደርጉት ፡ ብርታት ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በዘውድ ፡ በዓላችን ፡ ምክንያት ፡ በኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ሠርታችሁ፡ ያበረከታችሁልንን ፡ ቤት ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ይህም ፡ በእናንተው፡ ስም ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ፈቅደንላችኋል ።

528

የሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ሕዝብ ፡ ለሟቹኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጎዳር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እንደራሴ ፡ በክቡር ፡ ኮሎኔል ፡ ክፍሌ ፡ ዕርገቱ ፡ አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ እንደራሴው ፡ ክቡር ፡ ኮሎኔል ፡ ክፍሌ ፡ ዕርገቱና ፡ አቶ ፡ አክሊለ ፡ ደጀን ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ኮሎኔል ፡ ክፍሌ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

የሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መላው ፡ ሕዝብ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌም ፡ የሟቹኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ፡ ለማክበር ፡ በደኅና ፡ ላደረሳችሁ ፡ አምላክ ፡ ምስጋናውን ፡ እያቀረበ ፡ ለዚሁ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ የሕዝቡ ፡ መልክተኞች ፡ እነሆ ፡ ይዘው ፡ ቀርበዋልና ፡ የምስጋናውን ፡ ቃል ፡ አቶ ፡ አክሊለ ፡ ደጀን ፡ በንባብ ፡ እንዲያሰሙ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ የግርማዊነትዎን ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ እለምናለሁ ።

* * *

ለ) የአቶ ፡ አክሊለ ፡ ደጀን ፡ ንግግር ።

የዚህን ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቀውን ፡ የሟቹኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ፡ በዓልዎን ፡ የብር ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የሚያከብሩበትን ፡ ቀን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ከልብ ፡ የሚወድዎ ፡ የሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብዎ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በምናቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ መጀመሪያ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ አባትዎ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ቀጥሎ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለሐረርጌ ፡ አውራጃ ፡ ስለ ፡ ሀገሪቱ ፡ ልማት ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ኑሮ ፡ ማሻሻል ፡ የፈጸማቸውሉለትን ፡ በጎ ፡ ሥራና ፡ ድካም ፡ ሁሉ ፡ ለመዘርዘር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እንድናገር ፡ ለኔ ፡ ለታናሹ ፡ አገልጋይዎ ፡ ስለተፈቀደልኝ ፡ መሬት ፡ እየሳምሁ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናዬን ፡ አስቀድማለሁ ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

እጅግ ፡ የተወደዱት ፡ ጀግናው ፡ አባትዎ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ የሐረርጌን ፡ አውራጃ ፡ ገዥነት ፡ ሥልጣን ፡ ያገኙት ፡ የዳግማዊ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ወንድም ፡ በመሆናቸውና ፡ ወይም ፡ በደጅ ፡ ጥናት ፡ አልነበረም ። ዳግማዊ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሐረርጌን ፡ ከሰበሩ ፡ በኋላ ፡ አብረዋቸው ፡ ከነበሩት ፡ ከፍተኛ ፡ የጦር ፡ መሪዎች ፡ ውስጥ ፡ የሐረርጌ ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ሆኖ ፡ ለመቅረት ፡ የሚፈቅድ ፡ እንዳለ ፡ ቢጠየቁ ፡ አንድም ፡ እኔ ፡ ልቅር ፡ የሚል ፡ ስላልተገኘ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ የነበሩት ፡ ጀግናው ፡ አባትዎ ፡ ባላምባራስ ፡ መኰንን ፡ ጀግንነትና ፡ ቆራጥነት ፡ በተመላበት ፡ መንፈስ ፡ እንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ እኔ ፡ እቀራለሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ወንድማቸውን ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ይወዷቸው